# ሰዓቱ ደርሷል

ሰዓቱ ደርሷል መሰለኝ
ልቤን ሜዳ ሜዳ የሚለኝ
ገድላቸው ሲነሳ የሰማዕታት
የዳንኤል፡ የይስሃቅ፡ የክፍሉና የመኮንን
የሙሉጌታ፡ የአሉላ፡ የውብሸትና የሁሴን።

የህዝባቸውን ስቃይ በደል ማየት
አላስችል ብሏቸው በልጅነት
በ 14ና በ 15 ዓምት....ገና በጮርቃነት
ለፍትህ ሲጮሁ ለህዝብ መብት
ሲሰቃዩ በማእከላዊ እስር ቤት
ዕረገፉ ለአገራችን ነጻነት።

እየዘመሩ የትግሉ ነው ህይወቴ
ኢህአወሊ ድርጅቴ
ኢህአሠ ሠራዊቴ
ኢህአፓ ፓርቲዬ
አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መለያዬ
እያሉ ነበር የወደቁት
ገና በጥዋቱ የተሰዉት።

ደማችሁ ይጣራል ከተረሸናችሁበት መንደር
አጽማችሁ ደቆም ቢሰባበር
ግን ዛሬም አመፅ ይገንፍል አምርሮ
ሙስሊም ክርስቲያኑም ተባብሮ
ባንድ ላይ ይነሳ ባንድነት አብሮ።

በህዝብ የአመጽ ማዕበል
የወያኔን መሰሪ ተንኮል
ለመበጣጠስ ቆርጠው ተነስተዋል
በኢትዮጵያዊነት ምለዋል።

ክብር ለእግዚአብሔር
አላህ ወአክበር
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!!!

ጥር 2005
ከጎላ ምንጭ